Department *of* Human Service Programs
*Ellen Semonoff, Assistant City Manager*

City of Cambridge
51 Inman Street
Cambridge, MA 02139-1102
askdhsp@cambridgema.gov
voice: 617-349-6200
tty: 617-492-0235
fax: 617-349-6248

በ Cambridge ከተማ የDHSP የቅድመ-ትምህርት ቤት መርሃ-ግብሮች ላይ ላሳዩት ፍላጎት እናመሰግናለን! ልጅዎን ጥራት ባለው የቅድመ-ትምህርት ቤት መርሃ-ግብር ውስጥ በማስመዝገብ፣ ለመዋለ-ህጻናት እና ለብዙ ተጨማሪ ነገሮች እንዲዘጋጅ እየረዱት ነው። ከፍተኛ ጥራት ባላቸው የቅድመ-ትምህርት መርሃ-ግብሮች ውስጥ የሚሳተፉ ህጻናት የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ የተሻለ የሒሳብ ዕውቀት፣ ቋንቋ እና ማህበራዊ ክህሎቶች እንደሚኖራቸው ጥናቶች ያሳያሉ።

እባክዎ ልጅዎን የቅድመ-ትምህርት ዕጣ ውስጥ ለማስገባት www.cambridgema.gov/preschoollottery ላይ የሚገኘውን የኦንላይን የዕጣ ማመልከቻ በኦክቶበር ወር ውስጥ ሞልተው ያጠናቁ። በአካል ተገኝቶ እርዳታ የሚሰጥ ሰው በጥያቄዎ መሠረት ይገኛል። አስፈላጊ ከሆነ፣ እባክዎንdhsppreschools@cambridgema.gov ወይም 617-349-6254 ላይ ያነጋግሩ። ወቅታዊ፣ ትክክለኛ መረጃ እንዲኖረን እንዲሁም ዲሴምበር ላይ የዕጣውን ውጤት ለማሳወቅ እንድንችል ማመልከቻው ላይ የሚገኙትን ሁሉንም መረጃዎች አጠናቀው መሙላትዎ አስፈላጊ ነው።

ማመልከቻዎ እንደተጠናቀቀ እንዲታሰብ የኦንላይን ማመልከቻውን ከመሙላት በተጨማሪ ሌሎች ሰነዶችንም ማቅረብ ይጠበቅብዎታል። (አስፈላጊ ሰነዶች የDHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት የዕጣ ሂደት ወረቀት ላይ ተዘርዝረዋል) የ DHSP ቅድመ-ትምህርት ቤት የክፍያ መጠኖች የገቢ መጠንን መሠረት በሚያደርግ ተንሸራታች የዋጋ ልኬት ይወሰናሉ። የሚከፍሉትን የትምህርት ክፍያ መጠን ለማስላት እና ቤተሰቡ በአንዱ የመማሪያ ክፍላችን ውስጥ ቀዳሚ መቀመጫ ለማግኘት ብቁ መሆኑን ለመወሰን ሰነዶቹን እንጠቀማለን።

በሰብአዊ አገልግሎት መርሃ-ግብሮች መምሪያ ውስጥ መርሃ-ግብሮቻችን ለሁሉም የCambridge ቤተሰቦች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ እንተጋለን። Vouchers እንቀበላለን እንዲሁም ለትምህርት ክፍያ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች ስኮላርሺፖችን እናቀርባለን። ወቅታዊ የክፍያ መጠኖቻችንን እዚህ እሽግ ውስጥ ያገኛሉ። ገቢው 100% የ HUD አከባቢ አማካይ ገቢ ($126,200) ወይም ከዛ በታች የሆነ ማንኛውም ቤተሰብ ለትምህርት ክፍያ ድጋፍ ብቁ ይሆናል። የሚደረገው የትምህርት ክፍያ ድጋፍ መጠን ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ ብዛት እና የግል ችግርን መሠረት ያደረገ ነው። የCambridge ህፃናት ጥራት ያለው የቅድመ-ትምህርት እና ከትምህርት ሰዓት በኋላ የሚሰጥ ትምህርት ከማግኘት የቤተሰብ የሀብት መጠን ሊያግዳቸው እንደማይገባ እምነታችን ነው።

በኦንላይን ማመልከቻው ላይ የሚፈልጉትን ያህል ቅድመ ትምህርት ቤቶች እንዲመርጡ ይጠየቃሉ። ምርጫዎችዎን እንደ ምርጫዎ ቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ። እባክዎ የቅድመ-ትምህርት ቤት መቀመጫ ስለማግኘትዎ ማሳወቂያ ቢደርስዎ ልጅዎን የሚያስመዘግቡባቸውን መርሀ-ግብሮች ብቻ ይምረጡ። በከተማው ውስጥ ሰባት የቅድመ-ትምህርት መርሃ-ግብሮች ያሉን ሲሆን ሁሉም ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ናቸው። መርሃ-ግብሮቻችን በግዛቱ ከፍተኛውን የጥራት ደረጃ ተቀብለዋል እንዲሁም በ NAEYC (የታዳጊ ህጻናት ትምህርት ብሔራዊ ማህበር) በኩል ዕውቅናን አግኝተዋል።

ስለ ዕጣው ወይም ስለ ቅድመ-ትምህርት ቤቶቻችን ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን dhsppreschools@cambridgema.gov ላይ ወይም በ 617-349-6200 ያግኙጋግሩን። የዕጣ ማመልከቻ ሂደቱ ላይ

በቋንቋዎ እርዳታ ካስፈለግዎ፣ እባክዎ የቤተሰቦች ማዕከልን በ 617-349-6385 ያግኙ። በቅድመ-ትምህርት መርሃ-ግብሮቻችን ላይ ላሳዩት ፍላጎት በድጋሚ እናመሰግናለን። ከእርስዎ እና ከቤተሰብዎ ጋር አብረን ለመስራት በጉጉት እንጠብቃለን።

ከ ሰላምታ ጋር፦

Meghan M. White, Division Head
Childcare and Family Support (የህጻናት እንክብካቤ እና የቤተሰ ድጋፍ)